# ትል ነበር እማማ (ከያሬድ ተሾመ ኖርዌ)

ድሮ ባገር ቤቴ ፣
ከበን .. በገበቴ፣
በልተን .. ከሰታቴ፣
ትል ነበር ... እናቴ ...
ልጆቼ ብያቸው፣
ታሪክ የሌሌላቸው፣
አድገው ያስኮሩኝ፣
ቀን አይተው የካዱኝ፣
ሦስት ውሾች ነበሩኝ።

አንዱ! ... "ሰምቶ መቻል"
አለመጮህ ቀላል፣
ጠላቱ ቤት ገብቶ፣
ባይኑ ተመልክቶ፣
በጆሮው አዳምጦ፣
ጉዳቱን አላምጦ
በሆድ ማንገዋለል፣
በጭራው ማባበል፣
ቤት የለህም ቢባል! ..
የትም መንቀዋለል ...

ትል ነበር እማማ !
ከ 'ንቅልፋችን ቀድማ
አልብሳን ያን ሸማ
ከበን እንድንሰማ
ከታሪክ አውድማ
ትል ነበር እማማ !

ሌላው "መኮብለል"
መክዳት መማለል፣
መሄድ ሰው ማመን፣
መልመድ ባንድ ቀን፣
ማረድ ምሽንሽን፣
አዲስ መማማል።

ሰምቶ መቻል እዳ፣
መኮብለል ለማዳ፣
መሸምጠጥ ልኳንዳ፣
ጥቅማጥቅሙን አይቶ፣
የቀድሞውን ረስቶ፣
ሚሸሽ ከቤት ወቶ፣
ሚባች እኔን ትቶ፣
ከርሱን ተመልክቶ።

ትል ነበር እማማ ! ...
... በዚያ ባመሻሹ ... በዚያ በማለዳ፣
... ሰብስባን በጓዳ፣
... አስቀምጣን መደዳ ...

ሦስተኛው "ማን ደፍሮ"
ማን አልፎ በጓሮ፣
ሳይሰማ አምባ ጓሮ፣
ለማነቅ ጉሮሮ፣

ቀድሞ ነገር ጭሮ፣
በሁሉም አምርሮ፣
እኔ ብቻ ብሎ፣
ማነቅ ቀድሞ ዘሎ፣
ወንበር ተንጠላጥሎ።

ትል ነበር እናቴ ...
ከበን ከገበቴ፣
በልተን ከሰታቴ፣

በዚያ በደጉ ቀን ... ቀድማ በማለዳ፣
ሰብስባን በጓዳ፣
ታሪክ እንዳንከዳ፣
የሆዷን ከሆዷ፣

ውሻ ይደግ አለች ... 'ሚባል ማስተዋል
ህሉን 'ማይሰማ ... ሁሉንም 'ማይችል
ሁሉንም 'ማያምን ... ዋሽቶ 'ማይኮበልል
ዘሎ 'ማይናከስ ... ማን አለብኝ 'ማይል
ታሪክ 'ማይወቅሰው ... 'ሚባል ማስተዋል።